


http://www.hr2003.org

E-mail: passhr2003@hr2003.org Tel: 323-988-5688 Fax: 323-924-5563

========================================

## COMBINED ENGLISH AND AMHARIC TRANSLATION

**(Amharic translation follows English version below.)**

========================================

# Everything You Always Wanted To Know About H.R. 2003, But Were Afraid To Ask!

**"Defend Human Rights in Ethiopia. Help Educate All People on H.R. 2003. Share this "Frequently Asked Questions" (FAQs) with Everyone!"**

### What is H.R. 2003?

**H.R. 2003 (also known as "Ethiopia Democracy and Accountability Act of 2007") is a proposed law (House Resolution) in the U.S. Congress that is intended to promote democracy, freedom, human rights and accountability in Ethiopia.**

### How Does H.R. 2003 Promote Democracy, Freedom, Human Rights and Accountability in Ethiopia? Can You Give Me Specific Examples?

**Yes. H.R. 2003 promotes democracy in Ethiopia by providing financial and technical support to improve electoral procedures and ensure fraud free elections, offering specialized training programs to local, regional, and national legislative bodies (effective legislative techniques and processes), enhancing the capacity of political parties (organization building and management), and civil society groups (election**

**monitoring, voter egistration), professionalizing the National Election Board (electoral districting, voter, candidate, party registration rules and procedures, resolution of contested elections, voting irregularities), and encouraging peaceful resolution of disputes in society (dialogue, negotiations and compromise).**

**H.R. 2003 promotes freedom by encouraging the regime in power in Ethiopia to restore the democratic rights of the people recognized under international human rights laws and conventions and other laws in Ethiopia, removing all government press censorship and repealing specific restrictive press laws, and diversifying and strengthening private media in Ethiopia.**

**H.R. 2003 promotes human rights by strengthening human rights and civic society organizations, establishing permanent human rights monitoring and reporting processes, helping prosecute human rights abusers and bringing to justice all human rights abusers, including the killers of hundreds of innocent men, women and children, establishing a program which will provide legal support for all political prisoners and prisoners of conscience, and increasing the independence of the judiciary.**

**H.R. 2003 demands accountability for implementation of all of the foregoing by requiring the President of the United States to certify every six (6) months that the regime in Ethiopia is making progress in achieving the legislative objectives identified above.**

## Why is it important to have H.R. 2003?

**H.R. 2003 is important because it is the only realistic means of getting the ruling regime in Ethiopia to observe and abide by international human rights standards and respect the rule of law. Up to now, the regime has sneered at gentle persuasion, wagged its fingers at human rights organizations and defenders, laughed at the efforts of human rights groups and organizations that have attempted to "name and shame it" for its poor human rights record, turned a deaf ear to all reasonable pleas for improvements in human rights conditions, mocked, ridiculed and thrown sarcasm at members of the U.S. Congress who have made constructive efforts to help Ethiopia, devised and tried to use all forms of deception, duplicity, mendacity, disinformation, subterfuge and trickery to hoodwink the international community about its dismal human rights record.**

**The only thing that has scared the "pants off" the regime is H.R. 2003. For the first time in its 16 years of misrule in Ethiopia, the regime has realized what it means to be held ACCOUNTABLE! For the first time, this regime has come face to face with the generous American taxpayer who says loud and clear: "I do not want my hard earned taxes to support murderers, racketeers, thugs, hooligans and international outlaws."**

## What Happens if the Regime in Ethiopia Fails to Improve its Human Rights Record and Disregards the Requirements of H.R. 2003?

**If the regime in Ethiopia fails to improve its human rights record and disregards the requirements of H.R. 2003, non-essential aid (economic and other aid, EXCEPT humanitarian aid) will be suspended until such time the regime complies with international human rights standards. Humanitarian aid that will NOT be affected by H.R. 2003 include, among others, famine relief aid, emergency food aid and nutrition programs, disaster relief, health and vaccination programs, HIV AIDS and other medical assistance, malaria and infectious disease control, water and sanitation and many other similar programs.**

## How Would H.R. 2003 Work in Practice?

**The law will apply to suspend U.S. aid to Ethiopia ONLY and ONLY if is if the regime fails to meet specific human rights objectives, or does not make adequate general progress in their pursuit and achievement (e.g. release of all political prisoners, establishment and operation of an independent judiciary, prosecution of human rights abusers, operation of media without censorship, establishment of an independent national elections board, free operation of human rights organizations, etc.,). The law is very lenient and accommodating. If the regime fails to comply, the President of the United States could waive application of the law completely, regardless of the human rights situation in the country, if he deems it appropriate in the national interest of the United States. The bill has built-in grace period for compliance with its provisions.**

## Is the U.S. Congress Singling Out Ethiopia for Harsh Treatment in Considering H.R. 2003?

**No. There is in fact a very similar bill pending right now entitled the "The Vietnam Human Rights Act of 2007" (H.R. 3096) introduced by Cong. Chris Smith. In the past few years, the U.S. Congress has passed laws promoting human rights in various countries that have extremely poor human rights records. Last year, Congress passed the Darfur Peace and Accountability Act which, among other things, seeks to bring to justice persons in the Sudan guilty of war crimes. The Iran Freedom Support Act appropriates $10 million to support human rights groups in Iran. The North Korea Human Rights Act conditions future negotiations between the United States, North Korea, and other concerned parties on improvements in human rights. In the 2006 Foreign Relations Authorization Bill Congress imposed restrictions on military assistance to Indonesia until its government and military have cooperated fully with efforts to prosecute those responsible for human rights violations in East Timor.**

## Does H.R. 2003 Provide Any Money or Incentives to Ethiopia to Implement the Various Provisions?

**Yes. The bill appropriates a total of $40 million (or approximately $400 million birr) for two years (2008-2009) to implement the democracy, freedom, human rights accountability provisions.**

## Is There an Amharic Translation H.R. 2003?

**Yes. An Amharic translation of H.R. 2003 can be obtained at various websites dedicated to Ethiopian affairs. It may also be accessed at: http://www.hr5680.org/resources/hr2003_amharic.pdf**

## Is There One Organization That Pushes for Passage of H.R. 2003 in the U.S. Congress?

**No. There are numerous organizations and individuals who have worked extremely hard at the grassroots levels for passage of H.R. 2003. One of the many grassroots organizations dedicated to passage of this bill is the Coalition for H.R. 2003, which has an established website at: http://www.hr5680.org/ Various resources are available at this website for all interested in learning about H.R. 2003.**

## What Are the Main Arguments of Those Who Oppose H.R. 2003?

**The vast majority of people who oppose H.R. 2003 probably have not read or studied the provisions of H.R. 2003. For instance, former Harvard Prof. Ephraim Isaac, and Chairman of the "Shimagle" Committee that worked to get the Kality political prisoners released public stated that he had not read the bill, and lobbied against it in Congress publicly stated that he opposed the bill because he believed it would bring "slavery" and "colonialism" to Ethiopia. However, after reading it, Prof. Isaac declared that "there are very many good ideas in it."**

**Most opponents of H.R. 2003 (including the regime, its representatives and supporters) argue against the bill out of ignorance, lack of comprehension of the legislative language; or in some cases, out of willful disregard for the truth about the bill or driven by malicious intent to confuse and mislead the public.**

**Argument 1: The arguments against the bill are fourfold: The first is patently false, demonstrably bizarre and manifestly ridiculous. As Prof. Isaac asserted, H.R. 2003 will make Ethiopia a "slave" and a "colony" of the United States. Ethiopia has kept its freedom for 3,000 years, despite repeated European efforts to colonize it. It is impossible that one piece of legislation could "enslave" and colonize a country that**

**could not be "enslaved" or "colonized" when it was subjected to warfare by poison gas and the most destructive modern weapons.**

**Argument 2: The second argument is a bit more sophisticated, but equally laughable and misleading. The regime argues that the bill undermines Ethiopian sovereignty (full authority and power of the Ethiopian government in the country), and constitutes improper interference in the country's internal affairs. For a person who has not read the bill or has difficulty reading and understanding the legislative language, the argument may sound deceptively simple, and is cleverly misleading.**

**The argument is false and misleading for various reasons. The sovereignty issue is intended to distract attention from human rights issues to bogus issues of nationalism and resistance to foreign powers who want to meddle in Ethiopian affairs. The regime in power receives over $500 million from the U.S. government every year, and is said to be the third largest recipient of U.S. aid in the world. If the regime is true to its sovereignty argument, it has indeed fatally compromised it years ago by becoming hopelessly dependent on U.S. aid to supplement its budget, shore up its currency and the galloping inflation in the country, and run all sorts of economic and social programs using American aid.**

**The sovereignty issue to attack H.R. 2003 is part of the regime's distortion campaign because <u>in</u> <u>fact</u> the content of H.R. 2003 is similar or the same in language or spirit with the Universal Declaration of Human Rights, The International Covenant on Civil and political Rights and Articles 13-32 of the Constitution of Ethiopia.**

**In the final analysis, the fact of the matter is that he who pays the piper calls the tune. In H.R. 2003, America is saying to the regime, we want to hear the melodious song of democracy and human rights in Ethiopia for all of the hundreds of millions of dollars we give you every year; and we will even add an extra $40 million to hear that song sung in Ethiopia. If the musician does not want to sing the tune, then the musician should not ask or insist on being paid. It is just that simple!**

**Argument 3: The third argument, often made by regime officials, is that the bill "will hurt the country". They never tell you exactly how it will "hurt the country", but they often make that declaration. I challenge these officials or anyone to demonstrate how H.R. 2003 "hurts" Ethiopia in any form or shape. So should anyone who hears such nonsense.**

**Argument 4: The fourth argument is based on bravado. Opponents argue that external pressure on the regime from the U.S. Congress and/or the international community regarding improvements of its human rights record will not work, and that the regime will resist such pressures to maintain its national pride. If the regime is not concerned about U.S. pressure, why is it spending millions of dollars to lobby**

**against the bill in Congress? Why is it threatening to withhold the release of political prisoners if the Foreign Affairs Committee marks-up H.R. 2003.**

**The fact of the matter is the regime is feeling the heat like never before. The regime can huff and puff, and puff and huff; but unless it dramatically improves its human rights record, the voices of criticism and the demand for accountability will only increase and by leaps and bounds.**

## How Does the Regime in Power in Ethiopia Fight H.R. 2003 in the U.S.?

**The regime in power in Ethiopia has hired the third most powerful lobbying organization in the world, DLA Piper. This firm has over 3400 lawyers world wide, and in 2006, DLA Piper was ranked among the top 10 lobbying firms in the United States with U.S. lobbying income in excess of $16 million. The ruling regime in Ethiopia has paid DLA Piper USD$50,000 per month, plus hourly rates to defeat any kind of human rights bill in Congress.** If you really want to know how the government is fighting to defeat H.R. 2003 (or the former H.R. 5680) in Congress, check out this link: **http://www.publicintegrity.org/militaryaid/documents/FARA_Ethiopia.pdf**

**The regime also relies on its embassy in the United States, officials in the U.S. state Department and other individuals who have made efforts to mobilize certain powerful individuals and groups in the U.S. to oppose the bill.**

## Does the U.S. Have Legal Authority Under Its Own Laws to Impose Conditions on the Economic, Military and Other Aid it Provides to Ethiopia?

**Yes. Section 502B of the Foreign Assistance Act (1976, as amended) requires the secretary of state to transmit to Congress "a full and complete report" every year concerning "respect for internationally recognized human rights in each country proposed as a recipient" of U.S. security assistance. Specifically, this section requires information on specific areas such as: torture, arbitrary arrest, denial of fair trial and invasion of the home, extra-judicial killings or "arbitrary and unlawful deprivation of life, freedom of speech, press, religion and assembly, and freedom of movement and ability to participate in the political process. This section imposes restrictions on U.S. assistance to foreign governments that violate internationally recognized human rights.**

**22 U.S.C. 2304 provides: "The United States shall, in accordance with its international obligations as set forth in the Charter of the United Nations and in keeping with the constitutional heritage and traditions of the United States, promote and encourage increased respect for human rights and fundamental freedoms throughout the world… (2) Except under circumstances specified in this section, no**

**security assistance may be provided to any country the government of which engages in a consistent pattern of gross violations of internationally recognized human rights."**

## Where Can I Find an English and Amharic Translation of H.R. 2003 so That I can Read it Myself and Make Up My Own Mind?

**The following links will provide easy access to H.R. 2003 in English and Amharic.**
**The original bill can be found at its official website:**
**http://www.govtrack.us/congress/billtext.xpd?bill=h110-2003**
**An Amharic translation can be found at:**
**http://www.hr5680.org/resources/hr2003_amharic.pdf**

## When Will H.R. 2003 Pass And Become Law?

**There is no way to predict exactly when H.R. 2003 will pass. It all depends on the legislative process, and the efforts made by supporters of the bill in and outside of Congress. Recently, for instance, markup of the bill was delayed because Zenawi's regime took political prisoners hostage, and threatened the Foreign Affairs Committee that it will not release political prisoners if the bill is marked up. We expect many other tricks and shenanigans as the bill heads to the floor of the House and then to the Senate. The important thing to keep in mind is that all supporters of H,.R. 2003 must increase tenfold, twenty, a hundredfold to make sure the bill is successfully enacted into law.**

## Can You Tell Me in Simple Words the Process by Which a Bill Becomes Law in Congress?

**Yes. Generally, after a bill is introduced in either house (Senate or House of Representatives), it is referred to a committee for carefully study and examination. The Committee often refers the bill to a subcommittee for further study and analysis. The bill may be marked-up (amended) in subcommittee and reported back to the main committee, which will also perform its own mark-up process. If it passes in committee, the bill is sent to the floor for final debate and action. Once approved by the whole body, it is then sent to the other body (Senate or House) for further action. The versions of bill in the two Houses are reconciled in a conference committee, and the two houses vote on the identical bill. If it passes in both hosues, the bill is presented to the President for his signature, and upon signing becomes law.**

**For an excellent site that provides information on the Congressional legislative process, see http://www.vote-smart.org/resource_govt101_02.php**

## Where can I get official legislative information on H.R. 2003?

**One independent tracking source for H.R. 2003 is govttrack.us.congress. Visist the following link for current status of H.R. 2003.**
**http://www.govtrack.us/congress/bill.xpd?bill=h110-2003&tab=summary**

## What Can I Do to Help Pass H.R. 2003?

**There are many things you can do to help pass H.R. 2003. Before you can help us pass H.R. 2003, you must be fully informed about the bill and its provisions. Just as we do not want people to oppose H.R. 2003 without reading and understanding it, we equally do not want people to support H.R. 2003 without doing the same. Your support or opposition to the bill should be based on the facts, evidence and reasonable interpretation and construction of the legislative language.**

**The first thing you can do to help pass H.R. 2003 is to READ AND UNDERSTAND THE BILL AND FAMIIARIZE YOURSELF WITH ITS PROVISIONS. Once you have done that, there are many things you can do. Here are just a few examples:**

1) **Teach others about H.R. 2003, its human rights provisions and importance for Ethiopia.**
2) **Participate in grassroots advocacy by joining with others in telephone, fax, email campaigns.**
3) **Contact your congressional representative and ask him/her to cosponsor and vote for H.R. 2003.**
4) **Get your relatives, friends, coworkers, church/mosque/synagogue/civic organizations members, etc., to join in and help out by making phone calls, faxing, letters and so on.**
5) **Contact your local media (print and electronic) and get them to cover human rights issues, and write opinion pieces in your local papers.**
6) **Work with you state legislatures, particularly your local legislative representative and get a resolution on human rights in Ethiopia passed. Ethiopian Americans in Massachusetts and Oregon have already done it. A number of other states including California are pending.**
7) **Get the support of local human rights groups, unions and others for H.R. 2003.**
8) **Organize Congressional office visits (local districts and Capitol Hill) complete with issue papers, talking points, resources, etc.**
9) **Organize marches, events, activities, etc., in support of H.R. 2003.**
10) **Conduct panel discussions, conferences, workshops, community discussion forums (not only for Ethiopians but for all Americans) on H.R. 2003.**

11) **EXPOSE THE LIES ABOUT H.R. 2003, AND THE LYING LIARS WHO TELL THEM.**

## What Happens if H.R. 2003 is Not Enacted Into Law This Year?

**Nothing happens! Planet Earth will keep on spinning on its rotational axis. The sun will continue to shine. Congress will be back in session. AND WE WILL CONTINUE TO ADVOCATE FOR ETHIOPIA FREEDOM, DEMOCRACY AND HUMAN RIGHTS IN THE U.S. CONGRESS FOR AS LONG AS THE EARTH TURNS ON ITS AXIS, AND THE SUN CONTINUES TO SHINE.**




**http://www.hr2003.org**

***E-mail:*** ***passhr2003@hr2003.org*** ***Tel: 323-988-5688 Fax: 323-924-5563***

==================================================

# ስለሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 ማንኛውንም ነገር ለማወቅ ለምትፈልጉ፤ ገር ግን ለመጠየቅ የፈራችሁ

**ከረቂቅ ሕግ** 2003 **ተባባሪ ግብረ-ኃይል**
**Coalition for H.R. 2003**

**ትርጉም መላኩ ጸጋዬ መኮነን**

***"ለኢትዮጵያ ለሰብአዊ መብት ተሟገቱ ፤ ሁሉንም ሕዝብ ስለ ሰብአዊ መብት ድንጋጌ*** 2003 ***በማስተማር እርዳታ አድርጉ፤ በተደጋጋሚ ስለሚጠየቁ ጥያቄዎች ከሁሉም ጋር ተነጋገሩበት***!"

## ሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 ማለት ምን ማለት ነው?

***ሰብአዊ መብት ድንጋጌ*** 2003 ***እንደዚሁም "የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ እና የተጠያቂነት ድንጋጌ*** 2007"***በመባል የሚታወቀው ረቂቅ ሕግ በአሜሪካ ምክር ቤት ለውሳኔ የቀረበ ሲሆን ግቡም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ፤ነፃነት ፤ሰብአዊ መብትና ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ ነው ።***

## ሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 በኢትዮጵያ ዴሞክራሲን ፤ነፃነትን፤ ሰብአዊ መብትንና ተጠያቂነትን እንዴት ሊያሰጠብቀው ይችላል? ተጨባጭ ምሳሌ ልታቀርብልኝ ትችላለህ?

***በእርግጥ ሰብአዊ መብት ድንጋጌ*** 2003 ***በኢትዩጵያ ዴሞክራሲን ለማጠናከር የገንዘብና የቴክኒክ የሙያ ድጋፍ የምርጫ ሂደትንና ቅደም ተከተል እና ከማጭበርበር ነፃ የሆነ ምርጫ እንዲኖር ለቀበሌዎች፤ ለክፍለ ሀገራትና ለብሔራዊ ሕግ አውጭዎች የተለየ ስልጠና***

መርሃግብር በማዘጋጀት ውጤታማ የሆነ የሕግ ሙያና አሠራር እንዲኖር ያግዛል። የፓለቲካ ድርጅት (የአደረጃጀት ስልታቸውንና የአስተዳደር አሰራራቸውን) የሲቪል ህብረተሰብ ቡድኖችን (የምርጫን መቆጣጠር የድምፅ ምዝገባን) በመሳሰሉት በተገቢው በዴሞክራቲክ ሂደቱ እንዲሳተፉ። የብሄራዊ ምርጫ ቦርዱን ሙያተኞች እንዲይዙት ፤የምርጫ ወረዳዎች መራጮችና ተወዳዳሪዎች (እጩዎች) ፓሪቲዎች የምዝገባ ሕግና ቅደም ተከተል፤ የአወዛጋቢ ምርጫ ጣቢያዎች መፍትሄ አፈላለግ፤ የድምፅ አሰጣጥ ዝብርቅርቅነት እና ሰላማዊ የቅሬታ ማስወገጃ ስልትን ማበረታታት (ውይይት ድርድርና መቻቻል) እንዲጎለምስ ረቂቅ ሕጉ ያደርጓል።

ሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 በኢትዮጵያ በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ነፃነትን እንዲያከብር ማበረታታት፤ የዲሞክራሲ መብትም እንዲጠበቅና የአለማቀፍ ሰብአዊ መብትን ሕግጋቶችና ስምምነቶችን እውቅና እንዲሰጥ ፤ የኢትዮጵያ ሕጎች እንዲያከብር የፕሬስ ቅድመ ምርመራ መንግስታዊ ተቋማትን እንዲያነሳ፤ የፕሬስን ሕገ ገደብ ማስወገድ እና ፕሬሱ እንዲሰፋፋ በቁጥርም እንዲጨምር ብሎም የግሉ መገናኛ ብዙህን በኢትዮጵያ እንዲጠናከር ያደርጋል።

ሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 የሰብአዊ መብትን ይዞታ የሲቪኩ ማህበረሰብ ድርጅቶችና ሰብአዊ መብትን በማጠናከር ዘላቂነት ያላቸውን የሰብአዊ መብት መቆጣጠሪያና ዘገባ ማጠናቀሪያ ተቋማትን በመመስረት በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብትን በመጣስ ንጹሀን ሕፃናትን፤ ሴቶችንና ወንዶችን የገደሉትን ጨምሮ በሙሉ እንዲከሰሱና ለህግ እንዲቀርቡ እንዲሁም ለሁሉም የፓለቲካ እስረኞችና የሕሊና ታሳሪዎች የሕግ ድጋፍ የሚያገኙበትን መረሀግብር ማመቻቸትና ነፃ የፍትህ ስርአት ተቋማትን ቁጥርይጭምራል ።

ድንጋጌ 2003 ሰብአዊ መብት የተጠያቂነትን ጉዳይ በማንሳት የኢትዮጵያ ገዥ መደብ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሕግጋት እያከበረ መምጣቱንና በተግባር ማሻሻሉን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በየአመቱ አፈጻጸሙን በመከታተል ለሕግ አውጭው ምክርቤት እንዲያቀርቡ ይጥይቃል ።

## ለምን ይህ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 ጠቃሚ ሆነ?

የሰብአዊ መብት ድንጋጌ ረቂቅ ሕግ 2003 በጣም ለኢትዮጵያ ጠቃሚ ነገር ነው። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ገዥ መደብ የሕግ የበላይነትን ማክበሩንና አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ሕግጋት ለመጠበቁ ሁነኛ መከታተያ ዘዴ በመሆኑ ነው ።እስከ ዛሬ አገዛዙ የጨቆና መረቡን ትክክለኛ ገጽታውን በመሸፈን የማያቋርጥ የጭቆና ተግባሩን ቀጥሏል። ይህንን በሚቃወሙት በሰብአዊ መብት ድርጅቶችና ተሟጋቶች ላይ ጣቱን በመቀሰርና በማሾፍ ብሎም ስማቸወን በማጥፋትና ክብረ ነክ ተግባር በመፈፀም የሰብአዊ መብት ጥሰቱን ቀጥሏል። ደካማ የሆነ የሰብአዊ መብት ይዞታውን እንደያሻሻል የሚቀርብለትን ጥሪ ሁሉ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ በማለፍ የማታለሉንና በአሳዛኝ ሁኔታ የአሜሪካን ምክርቤት አባላትን ሳይቀር ሲፈልገው በማሾፍ ሳይሆን ሲቀር ደግሞ በዘለፋ የማጭበርበሪያ ዘዴወችን በሙሉ በመጠቀም ሁሉን መልክ ያዘለ ማታለልና ስህተትን በንግግር ሸፋፍኖ ማለፍ፤ ከእውነት

*ይልቅ ጥሩ ውሸት መዋሸትን በመምረጥ፤ የተምታታ መረጃ ማሰራጨትን ፤ የአለማቀፍን ሕብረተሰብ በማወናበድ የሚፈልገውን ለማግኘት በመጣር ላይ ነው።*

*ካለፉት* 16 *አመታት አገዛዙ የሚፈራውና ያገዛዙን ሱሪ ሊያስወልቀው እንደሚችል የሚሰጋው የሰብአዊ መብት ድንጋጌ* 2003 *ነው። በ*16 *አመታት የተዛባ አገዛዙ ለመጀመሪያ ጊዜ በፈፀመው ተግባር ተጠያቂነት እንዳለበት የተገነዘበው የአሜሪካ ግብር ከፋዮች በግልጽ እና በገሀድ ለገዳዮች፤ ለመዝባሪዎች፤ ለአመፀኞች፤ ለሕገ-ወጦችና አለማቀፍ ሕግጋት ለማያከብሩ ከላቤ የተወሰደ የግብር ገንዘብ እንዲሰጣቸው አልፈልግም፤አልፈቅድም ብለው ፊት ለፊት መጋፈጣቸው ነው ።*

## የኢትዮጵያ ገዥ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 በያሟላና የሰብአዊ መብት ጥሰቱን ቢቀጥል ምን ሊፈጠር ይቻላል?

*በኢትዮጵያ ያለው አገዛዝ የሰብአዊ መብት መጣሱን ቢቀጥል እና የሰብአዊ መብት ድንጋጌ* 2003 *መሰፈርት ባያሟላ የሚወሰደው እርምጃ ለመሰረታዊ የሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ባልሆኑ ተብለው በሚመደቡ የእርዳታ ስጦታዎች ላይ ማለትም የኢኮኖሚና የጦር መሳሪያ ሌላም ከሰብአዊ እርዳታ ውጭ ያሉት ሲቀሩ አገዛዙ የዓለም አቀፉን ሰብአዊ መብት ግዴታውን እስኪጠብቅ ድረስ እንዳይሰጡት ያደርጋል። የሰብአዊ እርዳታ በ*2003 *ድንጋጌ መሰረት ከማይቋረጡት መካከል የድርቅ ማስወገጃ እርዳታ፤ የአስቸኳይ የምግብ ፤ሰውነት የሚጠግኑ የምግብ አይነቶች፤ የአደጋ፤ የተፈጥሮ መአት መከላከያ እርዳታዎች፤ የጤናን የክትባት መርህ ግብሮች ብሎም የኤች አይቪ/ ኤድስን የህክምና እርዳታ የወባና የአካል መበከልን መከላከያ መዳህኒት፤ የተስቦ በሽታ መቆጣጠሪያ የውሃና የንፅህና መጠበቂያ እና ሌሎች ተዛማጅ መርህ ግብር ያላቸውን የእርዳታ አይነቶች አይመለከትም።*

## የሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 እንዴት በተግባር ላይ ይውላል?

*የአሜሪካ እርዳታ በኢትዮጵያ ላይ እንዲቋረጥ ለማድረግ ይህ ሕግ በስራ ላይ የሚውለው አገዛዙ በተወሰኑና በተመጠኑ የሰብአዊ መብቶች ተጨባጭ ጉዳዮች ላይ በተግባር ሳያውል የቀረ እንደሆነ ብቻ ነው።ወይንም በአጠቃላይ የሰብአዊ መብት ይዞታ ላይ መሻሻል እርምጃ ሳይወሰድ ሲቀር ነው። ለምሳሌ ሁሉንም የፓለቲካ እስረኞች ካልፈታ፤ ነፃ የሆነ የሕግ አካል ሳያቋቁም ሲቀርና በተግባርም ላይ ሳያውል ሲቀር ፤ የሰብአዊ መብት የጣሱ ግለሰቦችን ለፍርዱ እንዲቀርቡ ያላደረገ እንደሆነ፤ የመገናኛ ብዙሀን ያለምንም ቅድመ ምርመራ እንዲንቀሳቀሱ ካላደረገ፤ ነፃ የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋም ካልቻለና የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በነፃነት ተግባራቸውን እንዲያንቀሳቅሱ ካልፈቀደ እርዳታው እንዲታገድ ድንጋጌው ይጠይቃል።በአጠቃላይ ይህ ህግ በጣም የለዘበና ሁሉንም ሊያስተናግድ እንዲችል ተደርጎ የተቀመረ ድንጋጌ ነው ።*

*ይህ ሕግ የኢትዮጵያ ገዥ የሰብአዊ መብትን ይዞታውን የሚያሻሽልበትን የጊዜ ገደብ እንዲኖረው የተወሰነ የሙከራ ጊዜም ይሰጠዋል ምንም አይነት የሰብአዊ መብት ይዞታ ቢኖርም ቅሉ ለአሜሪካ ብሄራዊ ጥቅም አስፈላጊ ነው ብለው የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ካሰቡ ሕጉን ሊያግዱትና እርዳታ እንደበፊቱ እንዲቀጥል ሊያደርጉ ይችላሉ።*

## በሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 የተነሳ የአሜሪካ ምክር ቤት ኢትዮጵያን ነጥሎ ለከፋ ሁኔታ ይጥላታል ወይ ?

አይጥላትም። እንደኛው አይነት ተመሳሳይነት ያለው የሕግ ረቂቅ በአሁኑ ወቅት "የቬትናም የሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2007" (HR 3096) በመባል የሚታወቅ ደንብ በኮንግረስ ማን ክሪስ ስሚዝ አማካኝነት እየተካሄደ ነው። በአለፉት ጥቂት አመታት እንደዚሁ የአሜሪካ ኮንግረስ የሰብአዊ መብትን በማራመድ ረገድ ደካማ የሆነ የሰብአዊ መብት ይዞታ ለተመዘገበባቸው በርካታ ሀገራት ውሳኔ አስተላልፏል። ባለፈው አመት ምክር ቤቱ የዳርፉር ሰላም እና ተጠያቂነት ድንጋጌ አሳልፏል። በዚህም ውሳኔው ከበርካታ ጉዳዮች አንዱ በሱዳን የጦርነት ወንጀል የፈፀሙ ግለሰቦችን ለፍርድ ማቅረብ ነው። የኢራን ነፃነት ድጋፍ ድንጋጌም በኢራን የሰብአዊ መብት ለማጠናከር ለሚሰሩ ቡዱኖች 10 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ ተመድቦለታል። የሰሜን ኮሪያ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ በበኩሉ፤በአሜሪካና በኮሪያ የሚደረገውን የወደፊት ድርድር የተመረኮዘ ሆኖ ፤ሌሎች ይመለከተናል ለሚሉ ክፍሎችም ለሰብአዊ መብት መሻሻል የሚያደረጉትን ጥረት ያካተተ ነው ። ባለፈው 1998 ዓ.ም የአሜሪካው የውጭ ግንኙነት ኮሚቴ በኃላፊነት እርምጃ የወሰደበት እና ኮንግረሱም የተቀበለው የኢንዶኔሽያ መንግስትና ወታደሮች በምስራቅ ቲሞር ላይ ሰብአዊ መብት የጣሱት ለፍርድ እስከሚቀርቡ ድረስ በኢንዶኔሽያ ላይ የወታደራዊ እርዳታ ማእቀብ ጥሏል።

## የስብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 ለኢትዮጵያ ገንዘብ ይረዳል ወይስ የተለያዩ የማበረታቻ ድጋፎች ይሰጣልን?

እርግጥ ሕጉ በአጠቃላይ 40 ሚሊዮን ዶላር ማለትም ወደ 400 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር የሚገመት እርዳታ በሁለት አመት ውስጥ (2008-2009) በኢትዮጵያ (2000-2001) ለዴሞክራሲ፤ ለነፃነት ፤ለሰብአዊ መብቶች መከበርና ተጠያቂነት ለመሳሰሉት እቅዶች ተግባራዊነት መድቧል።

## የሰብአዊ መብትረቂቀ ሕግ 2003 በአማርኛ የተተረጎመ አለን?

አለ ።የሰብአዊ መብቱ ድንጋጌ 2003 የኢትዮጵያን ጉዳይ በሚከተሉት ድኅረ-ገፆች ወይም የኢንተኔት መረቦች በአማርኛ ተተርጉሞ ቀርቧል http://www. hr5680.org/resource /hr2003 amharic.pdf ላይ ማግኘት ይቻላል።

## በአሜሪካ ምክርቤት የሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 እንዲያልፍ የሚገፋ አንድ ድርጅት አለ?

የለም። በርካታ ድርጅቶችና ግለሰቦች በመሠረታዊ ደረጃ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 በምክር ቤቱ ህግ ሆኖ እንዲወጣ ብርቱ ጥረት የሚያደርጉ አሉ ።ከነዚህም በመሠረታዊ ደረጃ ከሚንቀሳቀሱት ድርጅቶች መካከል አንዱ ጥምር የሰብአዊ መብት ረቂቅ ሕግ 2003 የሚባለው ነው (Coalition for H.R. 2003) ይኸውም የኢንተርኔት ድኅረ-ገፆች አዘጋጅቷል

መረቡም ይኸውና http://www.hr5680.org የተለያዩ መረጃዎችና ጽሁፎች በዚህ ድኅረ ገጽ አማካኝነት ለማወቅ ለሚፈልጉ ሁሉ ተዘገጀቷል።

## የሰብአዊ መብት ረቂቅ ሕግ 2003 እንዲያልፍ የሚቃወሙት ግለሰቦችና ድርጅቶች መሠረታዊ መከራከሪያ ነጥባቸው ምንድን ነው?

በርካታ የዚህ ሕግ ተቃዋሚዎች ምን አልባትም የሕጉን ይዘት ያለነበቡ ወይንም የሚሰጠውን ጥቅም ያልተረዱ ናቸው።ለምሳሌ የቀድሞው የሀርቫርድ ፕሮፌሰር፤ የሸማግሌዎች ኮሚቴ ሊቀመንበርና የቃልቲ የፓለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ በመሰራት ላይ ያሉት ኤፍሬም ይሳቅ በሰጡት መግለጫ ሕጉን አለማንበባቸውን ገልጸው በተቃራኒዉ ግን ሕጉ እንዳይፀድቅ በአሜሪካ ምክር ቤት በግልፅ ዘመቻ በማድረግ ላይ ሲሆኑ እንደሳቸው እምነት ሕጉ "ባርነትን" እና "ቅኝ ተገዥነትን" ለኢትዮጵያ የሚያመጣ ነዉ ብለዋል። ፕሮፌሰር ይሳቅ ሕጉን ካነበቡት በኋላ ግን "በርካታ ጠቃሚ ጉዳዮችን አካቶ የያዘ ነዉ" ሲሉ ተናግረዋል።

ብዙዎቹ የሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 ተቃዋሚዎች (ገዥዎቹን፤ ተወካዮቹንና ደጋፊዎቹን) ጨምሮ ሕጉን ካለማወቅ በመነጨ የድንቁርና መንፍስ ይሞግቱታል፤ ስለ ሕጉ ድንጋጌ ጥልቅ የሆነ የቋነቋ አጠቃቀም ወይንም በአንዳንድ ሁኔታ እዉነቱንም እያወቁ ካለመቀበል ጋር በተያያዘ ሕጉን በማጣመምና ሕዝቡን በተሳሳተ አቅጣጫ ለመምራት በማሰብ የሚካሄድ ተቃውሞ ጭምር ነዉ።

ሕጉን በአራት መንገድ በመክፈል የማይስማሙ አሉ። የመጀመሪያው መንገድ በግልፅ ዉሸት እንግዳና ያልተለመደ ነገር በማስመሰል አሳሳች በሆነ መንገድ መግለፃቸዉ ነዉ ፤ልክ ፕሮፌሰር ይሳቅ እንዳሉት የሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 አሜሪካ በኢትዮጵያ ዉስጥ ባርነትን እና ቅኝ ገዥነትን እንድታመጣ ይረዳታል የሚል የሀሰት አነጋገር ነው ። ኢትዮጵያ ከአለፉት 3ሺህ አመታት ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች ሀገር ስትሆን በአዉሮፓ የተለያዩ የቀኝ ግዛት ወረራ ተሞክሮባታል። ለዘመናት በአደገኛ መርዝ በአጥፊ የጦር መሳሪያ ውርጅብኝ ተደብድባ ለቅኝ ግዛት ያልተንበረከከች ሀገር በአንድ ነጠላ ሕግ በባርነት ወይም በቅኝ ግዛት ትዉላለች ብሎ መገመት የሚያስገምት አነጋገር ነዉ።

2ኛው ያለመስማማት ጉዳይ ደግሞ በመጠኑ ወሰብሰብነት ያለዉ ነዉ። ግን እንደላይኛዉ የሚያሰቅ እና የሚያምታታ ነዉ ።አገዛዙ የሚለን ሕጉ የኢትዮጵያን ሉኣላዉነት ዝቅ የሚያደረግ ነዉ (ይህ ማለት የኢትዮጵያን መንግስት በሀገሪቱ ላይ ያለዉን ሙሉ ሰልጣን) እና በሀገሪቱ ውስጥ ጉዳይ ላይ አላስፈላጊ የሆነ ጣልቃ ገብነት የሚያመጣ ድንጋጌ ነዉ ይላሉ።የድንጋጌዉን ይዘት ለማንበብ ችግር ላለበት ሰዉ እና የህጉን ቋንቋ ለማይረዳዉ ይህ አይነት የተቃዉሞ ሀሳብ በጣም ቀላል ማታለያ ሲሆን እያወቁ ለመፈፀም ደግሞ በደንብ የተቀነባበረ ማሳሳቻ ዘይቤ ነዉ።

ያም ሆነ ይህ አይነት አሰተሳሰብ በሁሉም መንገድ የተሳሳተ ነዉ። የሉኣላዊነት ጥያቂ በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ላይ ያሉን ጥያቂዎች በብሄራዊ ስሜትና የዉጭ ሀይሎችን

ለመቋቋም የተደረገ እና የኢትዮጵያን ጉዳይ በትክክል መልክ እንዲታይ እየተደረገ ያለ የተሳሳተ አስተሳሰብ ነዉ።

የኢትዮጵያ ገዥ መደብ በየአመቱ ከአሜሪካ መንግስት $500 ሚሊዮን ዶላር ያገኛል ።ይኸውም አሜሪካ በዉጭ ሀገር እርዳታ ከምትሰጣቸዉ ሀገራት 3ኛ ደረጃ የያዘ ነዉ ።አገዛዙ በሉኣላዊነት ጥያቄ እውነተኛ ክርክር ካለዉ በብሄራዊ በጀቱ ላይ በአሜሪካ እርዳታ ላይ ለምን ጥገኛ ሆነ? ለምን የዉጭ ምንዛሬዉን አናረው ? በዚህም የተነሳ የዋጋ ግዝፈት በሀገሪቱ ላይ ወደቀ? እንደዚሁም ሁሉም የኢኪኖሚና የማህበራዊ ጉዳይ መረሀ ግብሮች በሙሉ በአሜሪካ እርዳታ ጥገኛ ሆኑ?

የሉኣላዊነት ጥያቄ አገዛዙ ያነሳው ሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 ለማጥቃት የማሳሳቻ ዘመቻ ነዉ ።ምክንያቱም የሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 መሰረታዊ ይዘት ከአለማቀፍ የሰብአዊ መብቶች አዋጅ ጋር ተመሳሳይ ቋንቋና መንፈስ ያዘለ ነዉ። የአለማቀፍ የሲቪልና የፓለቲካ መብቶች እንደዚሁም ከአንቀጽ 13 –32 ያሉትን የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ጋር ተመሳሳይ ነዉ።

በመጨረሻ አዝማሪ ለበላበት ይዘፍናል እንደሚባለው ሁሉ የአሜሪካ መንግስት ለገዥው መደብ የሚለው በየአመቱ በምንከፍለው አምስት መቶ ሚሊዮን ዶላር የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ዜማን መስማት እንፈልጋለን ይህንኑ ለማጠናከር የአሜሪካ ምክር ቤት $40 ሚሊዮን ዶላር በተጨማሪ ለመክፈልና ሰብአዊ መብት እንዲጠበቅ የማጠናከሪያ ድጋፍ ለመለገስ ዝግጁ መሆናችውን ነው እየገለፁ ያሉት ።የኢትዮጵያ መንግስት በሚያገኘው እርዳታ የሰብአዊ መብትን በሚገባ ካለከበረ ተጨማሪ ገንዘብ የሚሰጥበት መንገድ አሰፈላጊ አይደለም። ለምሳሌ ዘፋኖች ዘፈናቸዉን ከሙዚቃዉ ቃና ጋር በሚገባ አዋህደዉ ተመልካቹን ወይም አድማጭን ካላስደሰቱ ለምን ገንዘብ ይከፈላቸዋል አይነት ቀላል ጉዳይ ነዉ።

3ኛዉ መከራከሪያ በአገዛዙ ግልፅ የሆነዉ ሕጉ ሀገራቱን ይጎዳታል የሚል ሲሆን ሀገሪቱን እንዴት እንደሚጎዳት ግን ተናግረዉ አያዉቁም። ነገር ግን እየደጋገሙ ይህንኑ ያላዝኑታል።ማንኛዉም ባለስልጣናትም ሆነ ሌላ ይህ ሕግ እንዴት ኢትዮጵያን ሊጎዳት እንደሚችል የሚአብራራ የተጨበጠ ነገር የላቸውም በማንኛዉም መልኩ ይህንን አመለካከት ለማቋቋም ሁላችንም ዝግጁ ነን ።ለማንኛውም ማንም ይህንን አመለካከት ቁም ነገር ብሎ መቀበል የለበትም ።

4ኛው መከራከሪያቸዉ ደግሞ መሰረት ያደረገዉ ትክክለኛን ባህሪ ሽፈኖ በማስመሰል ላይ የተንተራሰ ነዉ።ተቃዋሚዎቻችን የሚሉን የአሜሪካ ምክርም ቤት ሆነ የሌላ አለማቀፍ ማህበረሰብ ዉጫዊ ግፊት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ይዞታ ለማሻሻል አይጠቅምም ።ምክንያቱም አገዛዙ ብሄራዊ ክብሩን ለመጠበቅ ሲል እቢተኛ ይሆናል ይላሉ ። አገዛዙ ስለ አሜሪካ ተፅእኖ የማያሳሰበዉ ከሆነ ለምን በሚሊዮን ዶላር በየጊዜዉ ነገር ፈጆች አሜሪካ ምክር ቤት ጉዳዩ እንዳይቀርብ እንዲ-ከላከሉለት ይከፍላል? ።ለምን ረቂቂ ህጉ ለዉጭ ጉዳይ የምክርቤቱ ኮሚቴ እንዳይቀርብ ፓለቲካ እስረኞችን በመያዣነት ለማቆየት ተጠቀመበት?

እዉነቱ ግን አገዛዝ ከመቸዉም በበለጠ የዚህ ግፌት እየለበለበዉ ይገኛል። አገዛዙ ባደረሰዉ ጭቆና የጣር ትንፋሽ በመተንፈስ ላይ ይገኛል። ነገር ግን የሰብአዊ መንቶች ይዞታዉን ካላሻሻለ በስተቀር የገዥ መደብ የተጠያቂነት ጉዳይ ተጠናክሮ በበለጠ ይቀርብለታል።

## በኢትዮጵያ በአገዛዝ ላይ ያለዉ ኃይል የሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 በአሜሪካ እንዴት ሊጻረረው ይቻላል?

ኢትዮጵያ ውስጥ በስልጣን ላይ ያለው ገዥ በአለም 3ኛ ደረጃ ላይ የሚገኘውን ጠንካራውን ዲ ላ ፓፐር (DLA Piper) የተባለውን ነገረ ፈጅ ድርጅት ቀጥሮ እየተሟገተ ነው። ይህ ነገረ ፈጅ ድርጅት በአለም ውስጥ 3400 የሕግ ባለሙያዎች ቀጥሮ በማሰራት ላይ ያለ ሲሆን ይኸው ድርጅትባለፈው 1998 ዓ. ም በአሜሪካ ከሚገኙ ጥብቅና ከሚቆሙ ድርጅቶች መካከል በከፍተኛ ደረጃ ከተመደቡት ከ10ሩ አንዱ ነው። የድርጅቱ ገቢ በነገረ ፈጂነት ብቻ በአሜሪካ $16 ሚሊዮን ዶላር በላይ ነው ።የኢትዮጵያው ገዥ ለዚሁ ድርጅት DLA Piper በየወሩ $50.000 ዶላር (ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጋ ብር) ይከፍላል። በተጨማሪ በየስዓቱ የሚከፈል ገንዘብን ጨምሮ በማንኛውም አይነት የሰብአዊ መብት የሚመለከት ሕግ ለማጣጣል እየሞከረ ነው ።

## በእርግጥ መንግስት ምን ያህል ሰብአዊ መብት ረቂቅ ሕግ 2003 ለማሸነፍ በምክር ቤት የሚያደርገውን ጥረት ለማወቅ በሚከተለው ድኅረ -ገጽ በመግባት ሊያረጋግጡ ይችላሉ።

ረቂቅ ሕጉን ውድቅ ለማድረግ አገዛዙ አሜርካ በሚገኘው ኤምባሲውና በአሜሪካን የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ባሉ ባለሥልጣናት እንደዚሁም በሌሎች በአሜሪካ በጣም ተሰሚነት ባላቸው ቡድኖችና ግለሰቦች አማካኝነት ሕጉን ለመጣል በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።

http://www.publicintegrity.org/militaryaid/docummenys/FARA Ethiopia.pdf

## አሜሪካ በኢትዮጵያ ላይ የኢኮኖሚ የወታደራዊ እና ሌሎች እርዳታ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ለመግባት የሚያስችል የራሷ የሆነ የሕግ ስልጣን አላትን?

እርግጥ አላት። በ1976 እ.ኤ.አ የተሻሻለው የአሜሪካን የውጭ እርዳታ ድንጋጌ በክፍል 502(B) ላይ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለምክር ቤቱ “የተሟላ ዘገባ” በየአመቱ እንዲያቀርብ ያዛል ።ዘገባው በአሜሪካ የደህንነት እርዳታ የሚያገኙ ሀገራት “በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘውን የሰብአዊ መብት አያያዝ ገቢራዊ አፈፃፀም ላይ” ያተኩራሉ። ይህ የሕግ ክፍል በተለይ ስቀቃን፤ በመደዳ የአፈሳ እስርን፤አግባብ ያለው የህግ አገልግሎት የተነፈጉትን፤ ከሕግ ውጭ የቤት ብርበራን ፤ከሕግ ውጭ ግድያን ወይም አድልዋዊ እና ሕገወጥ ግድያን ፤የመናገር ነፃነት፤ የመገናኛ ብዙሀንን ፤የሀይማኖት ነጻነት፤ የመሰብሰብ፤ ከቦታ ቦታ የመዘዋወር እና በፓለቲካ የመሳተፍ መብትን የተመለከተ ሲሆን ይህ ድንጋጌ

በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙ የሰብአዊ መብቶች ለሚፃረሩ የአሜሪካን እርዳታ ይከለክላል ወይም የተመጠነ እንዲሆን ያደርጋል።

22 የአሜሪካ የሕግ ሰንጠረዥ (US Code) በክፍል 2304 የሚለው "ዩናይትድ ስታትስ በአለም አቀፍ ደረጃ ባለባት ግዴታ በተባበሩት መንግስታት በተቋቋመው በ4ኛው ምዕራፍ እና ሕገ-መንግስታዊ ውርሱንና ባህላዊ ይዞታውን የሰብአዊ መብቶች መጠበቃቸውንም መሠረታዊ ነፃነት በመላ አለም መከበሩን.....

2ኛ በዚህ ክፍል በተለየ ሁኔታ ካልተብራራ በስተቀር ለማንኛውም ሀገር የደህንነት እርዳታ የሰብአዊ መብትን በተደጋጋሚ በሚጥሱና አለመቀፍ እውቅና የተሰጣቸውን በማይቀበሉ ላይ እርዳታ አይሰጥም" ይላል::

## እንብቤ እራሴን ለማንቃት እንድችል የሰብአዊ መብት ረቂቅ ሕግ 2003 የእንግሊዝኛና የአማርኛ ቅጅ የት ላገኝ እችላለሁ?

የሚከተሉት ድኅረ ገጾች ለሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 መረጃ በቀላሉ በእንግሊዘኛና በአማርኛ ማግኘት ይችላሉ ዋናውን ሕግ በራሱ ድኅረ ገጽ ማግኝት ይቻላል ይኸውም http://www.govtrak.us/congress/billtext.xpd? bill=h110-2003. የአማርኛው ትርጉም ደግሞ: http://www.hr5680.org/resounces/hr2003amharic.pdf.

## ሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 መቼ ነው ተቀባይነት አግኝቶ ሕግ ሆኖ የሚወጣው?

ረቂቅ ሕግ 2003 በዚህን ጊዜ ሕግ ሆኖ ይወጣል ብሎ ለመተንበይ አስቸጋሪ ነው ። ሕጉ በሕግ አወጣጡ ሂደት በሙሉ ሊወስን ይችላል። እንዲሁም ድንጋጌው በኮንግረስ የውስጥና የውጭ ድጋፎች ይወሰናል። በቅርቡ ለምሳሌ ደንቡ እንዳያልፍ መለስ ዜናዊ የፓለቲካ እስረኞችን መያዣ በማድረግ እንዲዘገይ አድርጓል ። ይኸውም ደንቡ በውጭ ጉዳይ ኮሚቲው ተቀባይነት አግኝቶ ከፀደቀ እስረኞችን እንደማይፈታ በመዛቱ የተነሳ እንዲዘገይ ተደረገ። በርካታ ማታለያ ዘዴዎችና ማጭበርበር አሁንም ሕጉ በምክር ቤቱና በሕግ መወሰኛው ምክር ቤት ሲቀርብ እንደሚሞክሩ ይጠበቃል። እዚህ ላይ በጣም ጠቃሚው ጉዳይ ሕጉ ፀድቆ እንዲወጣ የሰብአዊ መብት ድንገጌ 2003 ደጋፊዎች ቁጥር ከእለት ወደ እለት በመጨመር ከ10 በእጥፍ ወደ ሀያዎቹ ከመቶ ወደሁለት መቶ በማሳደግ ሕጉ እውን እንዲሆን ማድረግ ይቻላል።

## በምክር ቤቱ ይህ ሕግ እንዲጸድቅ የአሠራር ሂደቱን በአጭሩ ማስረዳት ይቻላል?

በአጠቃላይ ሕጉ (በሕግ መወሰኛው ምክር ቤት ወይም በተወካዮች ምክር ቤት) ቀርቦ ንግግር ከተደረገበት በኃላ እንደገና በጥንቃቄ ተጠንቶና ተመርምሮ እንዲቀርብ ለኮሚቴ ይመራል ።ይኸኛው ኮሚቴ በበኩሉ ወደ ንኡስ ኮሚቴ ለጥልቀት ጥናትና ትንተና ይልከዋል። በዚሁ ኮሚቴ ደረጃ ምን አልባት መሻሻል ያለበት ጉዳይ ካለ ተሻሽሎ ለጥናት ለመራው ኮሚቴ እንደገና ይመለሳል። ይኸኛው ኮሚቴ በበኩሉ የራሱን የማጠቃለያ ሀሳብ በመጨመርና በመቀነስ ያጠናቅቃል ።በእንደዚህ አይነት አሰራር በኮሚቴዎች ከለፈ በኃላ

ሕጉ ወደ ምክር ቤት መድረክ ይላክና ለመጨረሻ ክርክርና ውሳኔ ይቀርባል ።በመጨረሻም በድምጽ ብልጫ (በሁሉም አካላት) ተቀባይነት ካገኘ እንደገና ወደ ሌላኛው አካል (የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት) ለተጨማሪ እርምጃ ይላካል። የሕጉ አካል እንደገና በቤቱ የማመሳከሪያ ጉባኤ የሚባለው ኮሚቴ ይቀርባል ሁለቱም አካላት በሕጉ ላይ ውሳኔ ድምፅ ይሰጣሉ በሁለቱም ምክር ቤቶች ተቀባይነት ካገኘ ሕጉ ለፕሬዚዳንቱ ለመጨረሻ ይቀርባል በመቀጠልም ፕሬዘዳንቱ ከፈረሙበት ሕግ ሆኖ ይፀድቃል ማለት ነው።

ስለምክር ቤቱ የውሳኔ አሠጣጥ ሂደት በጣም ጥሩ መረጃ የሚሰጠው የሚከተለው ድኅረ ገጽ ይምልከቱ http://www.vote.smart.org/resource gov101 02.php

## በሰብአዊ መብት ረቂቅ ሕግ 2003 ግልፅ የሕግ መረጃ ከየት ነው የማገኘው?

ሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 ነፃ የመረጃ ማግኛ ድኅረ ገጹ govttrack.uscongress. ሲሆን አሁን ድንጋጌው የሚገኝበትን ወቅታዊ ሁኔታ ለማወቅ የሚከተለውን መረብ ይመልከቱ http://www.govtrack.us/congress/bill.xpd?bill=h110-2003&tab=summery.

## ሰብአዊ መብት ረቂቅ ሕግ 2003 እንዲያልፍ ምን ላደርግ እችላለሁ?

ሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 እንዲያልፍ ብዙ እርዳታ ማድረግ ይቻላል። ስለ ድንጋጌው ድጋፍ እርዳታ ከመስጠትዎ በፊት ስለ ሕጉ ይዘትና ስለሚሰጠው ጠቀሜታ በአግባቡ ሊያውቁ ይገባል። ሰዎች ሰብአዊ መብት ረቂቅ ሕግ 2003 ሳያነቡና ሳይገባቸው ሲቃወሙን እንደማንወደው ሁሉ በተመሳሳይ ስለ ሕጉ ሳያውቁ የሚደግፉንም እንደሚቃወሙን አይነት አንቀበላቸውም። የሕጉን ተቃዋሚዎች በተጨባጭ መረጃ ጭብጥና ምክንያት በተመላበት ትርጉምና የሕጉን የቋንቋ አጠቃቀም ገንቢነትም በማየት የመጀመሪያው ሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 ለመደገፍ ማንበብና መረዳት ሕጉ ጋር በቅርበት መተዋወቅ አስፈላጊ ሲሆን የሚሰጠውንም ጠቀሜታ ጠንቅቆ መለየት ያስፈልጋል። ይህንን አንድ ጊዜ ካደረጉ በኋላ በርካታ ነገሮች አሉ እርስዎም የሚፈፅሟቸው ለምሳሌ ያህል

1. ስለሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 ሌሎችን ማስተማር የሰብአዊ መብት ይዞታውንና ለኢትዮጵያ ጠቃሚነቱን ማሳወቅ፤
2. በየሚኖሩበት አካባቢ ከሚገኙ የረቂቅ ሕግ ደጋፊዎች ጋር በመተባበር በስልክ፤ በፋክስ፤እና በኢ ሜል ዘመቻ ማካሄድ፤
3. በየአካባቢ ያሉትን የአሜሪካ ምክር ቤት ተወካዮች ማነጋገር የሰብአዊ መብቱ ድንጋጌ 2003 ተባባሪ አዘጋጆች እንደሆኑ መጠየቅ፤
4. ዘመዶች፤ ጓደኞች፤ የስራ ባልደረቦች ቤተክርሲቲያንና መስጊዶች የማህበረሰብ መሰብሰቢያ ድርጅቶች (እድር፤ ማህበር፤ ሰንበቴ፤ የመሳሰሉት እንዲረዱ አባል እንደሆኑ በስልክ፤ በፋክስና በደብዳቤ መጠየቅ የመሳሰሉትን ተግባራት ማከናዎን፤
5. የአካባቢያችሁን የመገናኛ ብዙሀን ጋዜጦችና የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ (ሬዲዮ ቲቪ) የመሳሰሉትን በማነጋገር የሰብአዊ መብቶችን ይዞታ አስመልክተው ዝግጅት እንዲያቀርቡ አስተያየት በመፃፍ በየአካባቢ ጋዜጠኞች መሳተፍ፤

6. በየአካባቢያችሁ ካሉ ሕግ አውጭዎችና ተወካዮች ጋር የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ውሳኔ እንዲያገኝ ኢትዮጵያውያን አሜሪካን በማስቿሰስና በኦሪጎን የሚገኙት ይህንኑ አከናውነዋል። ሌሎች ግዛቶች ካሊፎርኒያን ጨምሮ ይኸው እየተካሄደ ነው ፤
7. የየአካባቢያችሁን የሰብአዊ መብቶች ቡድኞች ማህበራትና ሌሎችም የሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 እንዲደግፉ ማድረግ፤
8. የኮንግረስ ሰዎችን ቢሮ ድረስ ለማነጋገር ማለትም በወረዳና በዋና ከተማ ደረጃ ያሉትን እንደዚሁም የመነጋገሪያ ነጥቦችንና ደብዳቤዎችን ሌሎች መሠረታዊ መረጃዎችን በመሳሰሉት፤
9. ስላማዊ ሰልፍን የተለያዩ ዝግጅቶች በተግባር የሚታዩ ነገሮችን በማዘጋጀትና በመሳሰሉት የሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 መደገፍ፤

10. የፓናል ወይይቶችን ጉባኤዎችን ወረክ ሾፕ የየአካባቢ ነዋሪ ማህበረሰቦችን ማወያየት (የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን) መላ አሜሪካንና ሕዝብ ስለሰብአዊ መብት ድንጋጌ 2003 ማወያየት፤

11. የሰብአዊ መብት ድንጋጌን 2003 አስመልክተው የሚካሄዱ ውሸቶችን ማጋለጥ ይህንኑ ውሸት የሚነዙትንም በገሀድ መጠቆም።

## በዚህ አመትረቂቅ ሕግ 2003 ሕግ ሁኖ ባይፀድቅ ምን ይከተላል?

ምንም የሚሆን ነገር የለም ፤መሬት አሁንም በዛቢያዋ ላይ መሽከርከሯን አታቆምም፤ ፀሀይ ብርሀኗን መስጠቷን ትቀጥላለች፤ የምክር ቤት አባላትም ተመልሰው መደበኛ ተግባራቸውን በሚቀጥለው ዓመት ይጀምራሉ ።እኛም የኢትዮጵያን ነፃነት፤ ዴሞክራሲ እና የሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ በአሜሪካ ምክር ቤት መታገላችን ይቀጥላል። መሬት በዛቢያዋ እንደተመላለሰች ሁሉ ፤ፀሃይ ብርሀኗን እስከፈነጠቀች የእኛም የማያቋርጥ ትግል ይቀጥላል።